# ለቤተሰብ እንክብካቤ የሚወሰድ የሥራ ፈቃድ ህግ የስራ ቦታ ፖስተር

**የተሻሻለ፡ ሜይ 17፣ 2024**

Office of Human Rights
District of Columbia

## በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ያሉዎት መብቶች

### ለቤተሰብ እንክብካቤ የሚወሰድ የሥራ ፈቃድ

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ለቤተሰብ እንክብካቤ የሚወሰድ የሥራ ፈቃድ ህግ ሰራተኞች የሆኑ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ የ24 ሰአታት የእረፍት ፈቃድ (ከክፍያ ጋር ወይም ያለ ክፍያ) ወስደው ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዙ ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ይፈቅዳል። የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እነዚህን የሚያካትቱት ግን በነዚህ ብቻ ያልተገደቡ ናቸው። የወላጅ-የመምህራን ኮንፈረንስ፣ ኮንሰርቶች፣ ትእይንቶች፣ ልምምዶች፣ ስፖርታዊ ዝግጅቶች እና ልጁ/ልጅቷ ተሳታፊ ወይም የዝግጅቱ አካል እንጂ ተመልካች ያልሆነበት/ያልሆነችበት ሌሎች ፕሮግራሞች።

ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘው የፕሮግራም ቀን መገመት ካልተቻለ በስተቀር(*ለምሳሌ፡* የልጁ/ልጅቷ አስተማሪ አስቸኳይ የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባ እንዲጠራa መጠየቅ)፤ ሰራተኛው ከሚጠይቀው የፈቃድ ቀን 10 ቀናት በፊት ለቀጣሪው ማሳወቅ አለበት። ፈቃዱ ያለ ክፍያ ወይም ከክፍያ ጋር የቤተሰብ፣ የመዝናኛ፣ የግል፣ ማካካሻ ወይም የባንክ ፈቃድ ሊሆን ይችላል።

ፈቃድ መስጠቱ የአሰሪውን/ዋን ስራ የሚያደናቅፍ እና የምርት ወይም የአገልግሎት ክንውን ከወትሮው በተለየ አስቸጋሪ የሚያደረገው ከሆነ አሰሪው/ዋ ፍቃዱን ሊከለክል/ልትከለክል ይችላል/ትችላለ

### የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ትርጓሜ

አንድ ሰራተኛ እሱ፣ እሷ ወይም እነሱ የሚከተሉትን ከሆኑ ለዚህ ህግ ዓላማዎች እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ይቆጠራል፡

- የልጅ ተፈጥሯዊ እናት ወይም አባት፤
- ልጅን ለማሳደግ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ሰው፤
- እንደ የልጅ ሞግዚት የሚሰራ ሰው፤
- የልጅ አክስት፣ አጎት፣ ወይም አያት፤ ወይም
- ከላይ ከተዘረዘረ ሰው ጋር የተጋባ/ች ወይም አብሮ የምትየ/ሚኖር ግን ያልተጋባ ሰው።

### የአሰሪ ማስታወቂያ የመለጠፍ መስፈርቶች

አሰሪው/ዋ ይህንን ማስታወቂያ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ እና ማቆየት አለበት/አለባት። ይህን ማስታወቂያ በፍላጎቱ ሳይለጥፍ የቀረ አሰሪ፣ አሰሪው ማስታወቂያውን መለጠፍ ላልቻለበት እያንዳንዱ ቀን እስከ $100 ቅጣት እንዲከፍል ሊታዘዝ ይችላል።

ይህ ሰነድ በዲ.ሲ. የቀረበ መረጃ ሰጪ ወረቀት እና መመሪያ ነው። በዲ.ሲ. ላይ የተደረጉ የህግ ለውጦችን በተመለከተ የሰብአዊ መብቶች ቢሮ (OHR) የ1977 የሰብአዊ መብቶች ህግ (DCHRA) እና የ1999 የሰብአዊ መብቶች ማቋቋሚያ ህግ (HREA) ቢሮ። ይህ ሰነድ ለአንድ የተወሰነ ሁኔታ ለማመልከት እንደ ህጋዊ ምክር ሳይሆን ለትምህርት ዓላማዎች ብቻ ሊያገለግል ይችላል። የሕግ ምክር የሚያስፈልገው ማንኛውም ሰው ወይም አካል ጠበቃ ማማከር አለበት።

### የጥሰት ቅሬታን ማቅረብ

በዚህ ህግ መሰረት አሰሪው/ዋ ሚዛናዊ ሳይሆን/ሳትሆን ለቤተሰብ እንክብካቤ የሚወሰድ የሥራ ፈቃድ እንደነፈገ/ችህ ካመንክ/ሽ፣ ክስተቱ በተፈጠረ በአንድ አመት ውስጥ ለሰብአዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ቅሬታ ማቅረብ ትችላለህ/ትቺያለሽ። ቅሬታ ለማቅረብ፣ ይጎብኙ፡ እንዲሁም የዲሲ ሰባዊ መብቶች ቢሮ/OHR/ ሂደት የሚመለከቱ ጥያቄዎች በስልክ በ (202) 727-4559 ሊመለሱ ይችላሉ።

- **ኦንላይን** በ ohr.dc.gov፣ ወይም
- **በአካል** በ 441 4th Street NW, Suite 570N, Washington, DC 20001።

እንዲሁም የዲሲ ሰባዊ መብቶች ቢሮ/OHR/ ሂደት የሚመለከቱ ጥያቄዎች በስልክ በ (202) 727-4559 ሊመለሱ ይችላሉ።